**KINIJIT** NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT
**ORGANIZATIONS (KNAASO)**
766 Rock Creek Church Rd. NW
Washington DC. 20010
Tel: (202) 541 0556 Fax: (202) 541-0557 Email: kinijitna@kinijitna.org

## ጃንዋሪ 23 ቀን 2007 ዓ/ም
## የጋራ መግለጫ

## <u>የሰላምና የርቀ መንገድ የሚጀምረው የቅንጅትን መሪዎችና ሌሎች የዲሞክራሲ ተሟጋቾችን ያለ ቅድመ-ሁኔታ በመፍታት ነው።</u>

እንደ ኢትዮጵያ “ታዳጊ” ተብለው የሚጠሩ አገሮች ለልማትና ለተረጋጋ ህይወት ያላቸው ጉጉት እውን ሊሆን የማይችልበት አንዳችም ምክንያት የለም። ይሁን እንጅ ወደዚህ ራእይ የሚወስደው መንገድ ተፈጥሮ ባስቀመጣችውና እኛም ራሳችን በፈጠርናቸው መሰናክሎች የታጠረ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። መልካሙ ዜና ግን መሰናክሎቹ የቱን ያህል የተወሳሰቡ ቢሆኑም የሰከነ አመራር ካለ እድገትም የተረጋጋ ህይወትም ቅርብ ናቸው።

ገና ያልተገራ ይሁን እንጅ ሃገራችን ኢትዮጵያ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሃብት ክምችትና በእሴትነቱ ከዚያ የማይተናነስ የሰው ኃይል በረከት የተጎናጸፈች አገር ናት። ለኋላቀርነታችንና ለጎስቋላ ኑሯችን መነሻውም መድረሻውም የመልካም አስተዳደር እጦት መሆኑን ለማወቅ የቅርብ ጊዜ ታሪካችንን መቃኘት ብቻ ይበቃል። ከዚህ እውነታ በመነሳት ነው ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ለኢትዮጵያ ያለውን ራእይ የቀረጸው። የትግል አማራጩን ከነውጠኝነት ይልቅ ሰላማዊነትን፤ የኤኮኖሚ መርሁን ከመንግሥት ጣልቃ-ገብነት ይልቅ ነጻ ገበያን፤ የሕዝቦች ግንኙነትን በተመለከተ ከመከፋፈል ይልቅ በመከባበር ላይ የተመሠረተ አንድነትን፤ ሰብአዊ መብቶችን በተመለከተ በግለሰብ ነጻነት ላይ የተገነባ ዲሞክራሲያዊ ሥርአትን እንደመፍትሔ ያቀረበው። የቅንጅት ራእይና በጎ አመለካከት ላዲሲቷ ኢትዮጵያ መድህን ይሆናል ብሎ በማመኑም ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በ1997 ምርጫ ወቅት በነቂስ ወጥቶ የመረጠው።

የግንቦቱ ምርጫ በመላ አገሪቱ የጫረው ብሩህ ተስፋና አስደናቂ ብሔራዊ ስሜት የኢሕአዴግ መንግሥት በወሰዳቸው አሳዛኝ ርምጃወች የደበዘዘ ቢመስልም እንደገና ቦግ እንዲል ለማድረግና ሕዝባችን በሚመኘው የብልጽግናና የተረጋጋ የሕይወት ጎዳና እንዲጓዝ ለማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ አሁንም አለ። ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር በሀገራችን ዙሪያ የሚያንዣብቡትን አሳሳቢ ችግሮች ብቻ ሳይሆን ባሻገር የሚታዩትን ተስፋዎች ጭምር ያገናዘበ ስብሰባ ካካሄደ በኋላ የሚከተለውን የጋራ መግለጫ አውጥቷል።

1. የሃገራች የውስጥ ፖለቲካ በመንግሥትና በሕዝብ መሃከል ከፍተኛ መቃቃር የሚታይበትና የመንግሥት ወኪሎች በሕዝብ ላይ የሚያካሂዱት ወከባ ይበልጡን እየመረረ የመጣበት

ወቅት ነው። የዋጋ ግሽበት፤ የመብት ረገጣ፤ የነፃው ፕሬስ አፈና፤ ገበሬውና ሠራዊቱ ውስጥ የሚሰማው ሰቆቃ ከምንጊዜውም የበለጠ አስከፊ ሆኗል። እነዚህ ሁኔታዎች ባስቸኳይ ካልታረሙ አሳሳቢ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ቀውሶች መከሰታቸውና የሃገሪቱ ህልውናም ሆነ ልኡዋላዊነት አደጋ ላይ እንደሚወድቅ አንጠራጠርም።

2. ኢትዮጵያ የምትገኘው የፖለቲካና የሃይማኖት ትርምስ በገነነበትና ታላላቅ መንግሥታት በሚፋለሙበት አጥቢያ ነው። በዚህም የተነሳ ብሔራዊ ጥቅሟን የሚያስጠብቅ በሳልና ዘላቂነት ያለው የዲፕሎማሲ ፖሊሲ መከተሏ አማራጭ የለውም። ለዘመናት ጸንታበት የቆየችውን ገለልተኛ የፖለቲካ መሥመር ስታ አላስፈላጊ ጦርነት ውስጥ እንድትገባ የሚደረግ ከሆነ ማለቂያ በሌለው ውዝግብና አድቃቂ ወጥመድ ውስጥ ልትወድቅ ትችላለች። ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከሶማሊያ ግዛት ባስቸኳይ የምውጣቱ ጥያቄ ወሳኝ ነው። ይልቁንም ጎረቤት አገሮች በየአጥቢያቸው ሠላምና መረጋጋትን ለማምጣት በሚያደርጉት ጥረት ውስጥ ገንቢ ሚና በመጫዎት የታላቅ ውንድምነት ግዴታችንን መወጣት ይኖርብናል እንላለን።
3. በሃገር-በቀል ነባራዊ ሁኔታዎችም ሆነ በዓለም አቀፍ ተጽእኖዎች ግፊት የሚከሰቱ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት የኢትዮጵያን ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብት የሚያከብር፤ በሕዝቦች መሃከል እኩልነትን የሚያረጋግጥ ሚዛናዊ ያስተዳደርና የፍትህ ሥርዓት ሲዘረጋ ስለሆነ ይህን ሥርአት ለመገንባት የምናደርገው ጥረት ከምን ጊዜውም በበለጠ ሊጠናከር ይገባል። የ 1997 ምርጫ ያመላከተው መሥመርና የከፈተልን ተስፋ እጅግ በጣም ብሩህ እንደነበረ ስናስታውስ ጅምሩን ከዳር ለማድረስ የምንቀጥበው ጉልበት ሊኖር እንደማይገባ ያሳምነናል።
4. በሃገር ውስጥ ሰላም እንዲሰፍንና ውጥረት እንዲረግብ ሊወሰዱ የሚችሉት ርምጃዎች የሚጀምሩት በፈጠራ ክስ ለሥራት የተዳረጉትን የቅንጅት መሪዎች፤ የሕዝብ ተመራጮችና ሌሎች የደሞክራሲ ተሟጋቾች ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ በመፍታት ነው። የኢሕአዴግ መንግሥት ሊከተል የመረጠው የፖለቲካ መሥመር የውስጡንም የውጩንም ከበሬታ ስላላስገኘለት የሠላምና የርቅ ጎዳናን ባስቸኳይ እንዲሻ አጥብቀን እንጠይቃልን።
5. ሰሜን አሜሪካ የሚገኘው ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊ-አሜሪካዊ ሕብረተሰብ በሚኖርበት አገር የተጎናጸፈውን የነፃነትና የመብት በረከት ለናት አገሩና ለወገኑ ለመመኘቱ፤ ይህም እውን እስኪሆን ድረስ የማያሰልስ ትግል ለማካሄድ የቀረጠ ለመሆኑ ምስክር የሚያሻው አይደለም። ዕውቀቱን፤ ጊዜውንና ገንዘቡ ሳይቆጥብ የዲሞክራሲ፤ የመብትና የአንድነት ተሟጋች መሆኑን አስመስክሯልና።

ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር
ዋሺንግተን ዲሲ
ጃንዋሪ 23ቀን 2007 ዓ/ም
www.kinijitna.org